# ሰሞኑን በፓልቶክ
# ቁጥር 6
# ከፍርሃት የመነጨ ጥላቻ

ከበልጅግ አሊ

እኔም ሰሞኑን ጠፍቼበት ከነበረው የፓልቶክ ፍልሚያ አደባባይ ብቅ ብዬ የተለወጠ ካለ ስመልከት አንድ ያገኘሁት ቢኖር የስድብ መለኪዬን ከነበረበት ክፍል አንስቼ ወደ ወያኔ ቅጥረኞች ሸንጎ ሲቪሊቲ ወደሚባለው የሆዳሞች ስብስብ ክፍል ወስጄ እንዳስቀምጠው ተገድጃለሁ። በዚህ ክፍል በስድብ መለኪያዬ ኢህአፓና ቅንጅት ከፍተኛውን የስድብ ውርጂብኝ ሲያገኙ ፣ ሰለሞን ተካልኝ የወያኔን ጠበል በመጠመቁ ሲሞገስ ነበር። ልደቱ እራሱ ወያኔ ስለነበር ብዙም አልተደነቀለትም እንጂ እዚሁ ክፍል በመቅረብ ታማኝነቱን ገልፅዋል።

አንድ በጣም እራቅ ብለው የሚኖሩ በጣም የማከብራቸውን ግለሰብ በሰልክ ስለ አገራችን ሳወራቸው ሳለ አንድ ጥያቄ አነሳሁባቸው። ለምንድነው ወያኔም ከሁሉም ተቃዋሚዎች ኢሕአፓን የሚጠላው? ብዬ ብጠይቃቸው ያሉኝ መልስ ትዝ ይለኛል።

የወያኔ ጥላቻ ከባድ ነው ከፍርሃት የመነጨ ጥላቻ ነው። ወያኔ ከማንኛቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች በላይ ኢሕአፓን ይፈራል። ኢሕአፓ በትግራይ ሳይቀር ያለውን የህዝብ ድጋፍ ወያኔ ጠንቅቆ ያውቃል። የኢሕአፓ አባላት ቆራጥነትን ለሃገር ተሰዊነትን ወያኔ አያጣውም። ስለዚህም ነው ወያኔ የኢህፓን አባላትን እነ ጋይምን የገደለው እነ ደብተራውን በድብቅ እስር ቤቱ የሚያንገላታው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ኢሕአፓ ወያኔን በደንብ ያውቀዋል። ወያኔ የሚጠቀምባቸውን የመከፋፈያ ዘዴዎች ቀድሞ ያጋልጠዋል። በዚህና ሌሎች በዚህ የመሳሰሉ ምክንያቶች ነው ወንድሜ ብለው አሰረዱኝ።

ይህን የወያኔ የፓልቶክ ክፍል ያየ፣ በክፍሉ የተሳተፈ፣ እንደሚያውቀው ወያኔ ዛሬ ከመቸውም የበለጠ ፍራቻ ላይ መሆኑን ነው የሚገነዘበው። ምድረ የወያኔ ሚኒስተር በየሳምንቱ እየቀረበ ወያኔን አጣፍጦ ለማቅረብ ይሞክራል። የኢኮኖሚው እድገት ይወሳል። አዲስ ሰለተፈጠሩት ሀብታሞች በብሄረሰብ ደረጃ ስንት ሊደርሱ እንደሚችሉ ሲነገረን ነው የከረምነው። ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን እንደተባለ በተከፈላቸው የወያኔ ቅጥረኛ ፕሮፖጋንዲስቶች በችግር ላይ ስለሚገኘው ህዝብ አይጠቀስም ። ስለስራ አጡ አይወራም። ስለመብራትና ውሃ ማንም አያነሳም። አንዳንድ የዋህ ቅን አንጆቶች ከመጡ መድረክ ይሰጣቸውና ምድረ ወያኔ ተሰብስቦ ይሳለቅባቸውል። ተስፋ አይቆርጡም እየተመላለሱ አላማቸውን ለማስረዳት ይሞክራሉ። እነዚህ የዋሆች ያልገባቸው ቢኖር ቅጥረኞቹ ተከፍሏቸው የሚሰሩ አፈ እሳት ፕሮፖጋንዲስቶች እንደሆኑ ነው።

ወያኔ ከግንቦቱ ምርጫ በፊት እንኳን ለኛ ለፓልቶክ አባላት ለድርጅቶችም የእርቅ ጥሪ ከመጤፍ አይቆጥረውም ነበር። ታዲያ ምን ሆነው ነው እነዚህ የወያኔ ቅጥረኞችና አባሎች ወደ ፓልቶክ ብቅ ያሉት? ይህንን ጥያቄ ሁላችንንም ልንጠይቀው ይገባል። ለኔ መልሱ ግን አንድ ነው ። **ፍርሃት**።ከስልጣን የመወገድ ፈርሃት፣ ከህዝብ የዘረፉትን ነዋይ የማጣት ፍርሃት ፣ ለፍርድ መቅረብ ፍርሃት ፣ በእጃቸው ላይ ያለው የሰው ደም ፍርሃት ፣ በግንቦቱ እንደታየው የህዝብ የአንፈልግም አመፅ ማዕበል እንደገና መነሳት ፍርሃት ፣ የግንቦቱ እንቅልፍ የሌለባቸው ሌሊቶች መደገም ፍርሃት ፣ አስፈሪው የህዝብ አልፈልግም ባይ የዝምታ አድማ ፍርሃት፣ እንዲሁም እናንተ ልትጨምሩባቸው የምትችሉት ብዙ ብዙ ፍርሃቶች ። እነዚህ ፍርሃቶች ናቸው ያ በትዕቢት ተወጥሮ ጠንካራ ተቃዋሚ እፈልጋለሁ ሲል የነበረው ፣ ጫካውም ያውላችሁ ግቡበት ሲለን የነበረው ወያኔ ዛሬ ሚኒስተሮቹ 100 ለማይሞሉ ደጋፊዎቻቸው በየፓልቶኩ እየላከ ቅስቀሳቀውን የተያያዘው። ያኔ እንደልቡ ሲንደላቀቅብን የነበረው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወያኔ የተጠቀመባቸው የመከፋፈያ ዘዴዎቹ ሁሉ ዛሬ አልሰራም ስላሉትና ሕዝቡ በአንድ ላይ ስለተነሳበት ጭንቀትና ፍርሃት ውስጥ የገባው።

በየፓልቶኩ የተመደቡት የወያኔ ካድሬዎች በኤርትራ በተቋቋመው ህብረት ምክንያት በተፈጠረው ቅራኔ በመጠቀም  በየክፍሉ እየዞሩ ይህን የፍርሃት ጥላቻ ፕሮፖጋንዳቸውን ተያይዘውትም ነበር። ለምሳሌ ቅንጀትን የሚደግፉ  ክፍል ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አባላትን ልብ ለመሳብ የቅንጂት አባል ነን በማለት ኢሕአፓ  ላይ ጥላቻውን ይነዙ እንደነበርና( አፕሪል የሚባለውን እናስታውሳለን)፣ በዚህም ክፍል ታላቅ ተሰሚነት አግኝተውም እንደነበር የሚታወስ ነው። አሁን እነዚህ የወያኔ ካድሬዎች እራሳቸው ክፍል ከፍተው በግልፅ ሲወጡ ምን ያህል የሚያሳዝን ነው። ማንስ ተቃዋሚዎችን ይከፋፍል እንደነበር ግልጽ አደለም? ዛሬም ቢሆን በዚህ ክፍል ያሉ አንዳንዶቹ ይህንን ወያኔዎች የጀመሩትን ኢሕአፓን የመሳደቡን ተግባር ከማስፋፋት አልተቆጠቡም። ይህ ወያኔን የሚደግፍ ተግባር ሊቆም ይገባ እንደነበር በክፍሉ አንድ ቀን በተገኘሁበት ቀን ሲወሳም ነበር። ግን ሁኔታው ቀነሰ እንጂ አልቆመም ። እነዚህ የወያኔ ካድሬዎች በሌሎቹ ክፍል እየሄዱ በኤርትራ ስለተቋቋመው ህብረት እያነሱ ጠቅላላ ቅንጀትን ብሎም የግንቦቱን ድል እንድንሰድብ ይገፋፋሉ። በኤርትራ የተቋቋመውን ህብርት ወያኔ ለተቃዋሚዎች መከፋፈያ ሊጠቀምበት መንገድ መከፈት የለበትም። አሁን ሁኔታውም ስለሰከነ ተቃዋሚዎቹ ሌላ መንገድ ሊፈልጉለት ይገባል እንጂ ለወያኔ ሴራ መንገድ ሊሰጡት አይገባም።

ወያኔ በጣም ተጨንቆአል፣ መግቢያ አጥቶአል፣ ፍርሃት አለበት፣ ያ ፍርሃቱ ሕዝብን እንዲጠላ፣ እንዲገድል፣ እንዲያስር፣ እንዲያፍን ፣ አድርጎታል፣ ተራ የሆነ የመከፋፈል ስራው አልተሳካለትም። ሰለዚህም በአገኘው ሁሉ ተቃዋሚዎችን ለመከፋፈል ጥረት ያደርጋል። የቻለውን በገንዘብ ይገዛል። ያልቻለውን ያጥላላል። ህዝቡን በዘር ለመከፋፈል ይሞክራል። ያ ስለአልተሳካለት ሰሞኑን ደግሞ በሃይማኖት ተያይዞታል። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን መርዝ የተሞላበት ተንኮል በድል እንደሚወጣው አልጠራጠርም።

በዚሁ በፓልቶክ ክፍል ወያኔ ሰለሞን ተካልኝን፣ ልደቱ ክህደቱን፣ የመሳሰሉትን በማቅረብ ሌላ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ተያይዞአል። ሰለሞን ተካልኝ ምነው እሱ ላይ ከረምክበት አትበሉኝ እንጂ ይህን እድል በመጠቀም ለከበርቴ አላሙዲን ለሚሌኒየም ስራ የመጠየቂያ ማመልከቻውን ሽራተንን በማወደስ አቅርቦል። ሰለሞን የስራ ባልደረቦቹን ወቅሶአል። ወያኔ እንደጨነቀው ፣ ፍርሃቱ እንቅልፍ እንደነሳው የምናውቀው በዚህ ነው። ማንም ይሁን ማን ተቃዋሚዎችን ከተሳደበ፣ ከታሰሩት የቅንጅት መሪዎች ጋር ቅራኔ ውስጥ ከገባ ፣ ኢሕአፓን ከተሳደበ፣ ወዳጁ ነው።

ወያኔ ሚሌኒየምን በማዘጋጀት የአጣውን የህዝብ ድጋፍ አለኝ ብሎ በውጭ መንግስታት ለማሳየት ጥረት ላይ ነው። ተቃዋሚዎች ይህንን እኩይ ተግባሩን እንዳይቃወሙት ሬድዮ በመክፈት፣ በፓልቶክ በመገኘት ተቃዋሚዎችን እየከፋፈለ ቢሆንም ሁሉም ተቀዋሚዎች ለወያኔ ሚሌኒየም ዝግጅት ጥሩ አመለካከት ስለሌላቸው ተቀባይነት አላገኘም። ግን አለመቀበል ሌላ ነገር ሲሆን ዝግጅቱን ለተቃውሞ ማዘጋጀት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ባለፈው እንደጠቀስኩት ብዙ ነገር መስራት ባይቻል እንኳን የኡኡታ ተቃውሞ ማሰማት ይችላል። ወያኔ ገና ይህንን ማሰባችንን ሲሰማ ፍርሃት ይሰማዋል። ምድረ ሆዳም ሁሉ ይደነግጣል ። ተቃዋሚዎች በዚች ጉዳይ ላይ እንኳን ተስማምተው ቅስቀሳው ከአሁኑ ቢጀምሩ ወያኔና ደጋፊዎቹን ጥሩ ቤት ስራ እንሰጣቸዋለን። ለዚህም ህብረቱ አላፊነቱን ወስዶ ዝግጅቱን ከሌሎች የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ቢጀምር ጥሩ ይሆናል እላለሁ። የፓልቶክ ክፍሎችም ይህንን ሃሳብ በማስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዚህ በፊት ታስበው የነበሩት የሁሉም ፓልቶክ ክፍሎች ስብሰባም ውጤታማ ቢሆን ታላቅ የሆነ ስራ ሊሰራ ይችላል።

**ሚሌኒየሙን እነርሱ በውስኪና በሆዳም ዘፋኞች እኛ ደግሞ ከሞቱብንና ከታሰሩብን ጋር በጩኸት እናሳልፍ።**

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com